# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

***Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)***

(አንድነት/United)


## እንኳን ደስ ያለን!

ሐምሌ ፳፮ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ. ም
August 2, 2018

ሰላም ለሰው ልጅም ሆነ ለፍጥረታት ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሰላምን ለማግኘት የሚከፈለውን ዋጋ በአሃዝ መተመን አይቻልም። ሰላም ላይ ለመድረስ የሚኬደው መንገድ፣ ረዥም፣ አድካሚና ጠመዝማዛ ነው። ሰላምን ለማምጣት ትዕግሥት፣ ጥበብና ከፍተኛ ጽናትንም ይጠይቃል። ሰላም ሲኖር ሰዎች የተረጋጋ ሕይወት ይኖራቸዋል፣ ቤተሰብም ጥሩ ሕይወት መምራት ይችላል፣ ሀገርም በልማት ጎዳና ላይ መጓዝ ትችላለች።

በአንዲት አገር ውስጥ ሰላም ካለ ኅብረተሰቡ ምርት ያመርታል፣ በተለያዩ ዘርፎች አገልግሎቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ያደርጋል፣ አገርንም ያለማል፣ ያሳድጋል። ሰላም ሲኖር በፖለቲካው ይሁን በሃይማኖት ወይም በሌሎች ጉዳዮች የተነሳ በጥላቻ ከመፈላለግና ከመገዳደል ይልቅ ዓላማዎችንም ሆነ ዕምነቶችን በመከባበር ማራመድ ይቻላል። የፖለቲካው አየር ሲደፈርስ ግን የኅብረተሰቡን በአጠቃላይ፣ በተለይም ደግሞ የቤተሰብን ሰላማዊ ሕይወት ያውካል። የአገር ኤኮኖሚም በዚያው ልክ ይቀጭጫል። ስለሆንም ሰላም ለቤተሰብ፣ ለማኅበረሰብና ለአገር ግንባታ እጅግ ተፈላጊ ነው።

በሃገራችን ውስጥ ባለፉት 27 ዓመታት ሰላም በማኅብረሰባችን፣ ሰላም በሃይማኖት አባቶችና አማኞች ዘንድ ጠፍቶ፣ ሕዝባችን በአካል፣ በመንፈስና በሕይወት ከፍ ያለ ዋጋ ሲከፍል ቆይቷል። ለሰላም እጦት ዋናው ምክንያት የኢህአዴግ/ህወሓት አገዛዝ ነበር።

ህወሓት ገና ሥልጣን እንደያዘ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የበላይ ጠባቂ የሆኑትን ፓትሪያርክ ከቀኖና ቤተክርስትያን ውጭ፣ በአገዛዙ ትዕዛዝና ማስገደድ፣ ከአገር አባሮ የሰላም ቤት የሆነችው ቤተክርስቲያ በሁለት ተከፍላ እንድትታመስ አደረገ። ዓለም በቃኝ ብለው የተሰደዱ መነኮሳት በአገዛዙ ካድሬዎች ከገዳማቸው ተባረሩ፣ ታሰሩ፣ እንዲሁም


**P.O.Box 91384**
**Los Angeles, CA 90009**
**Phone: 202- 241 2078**
**eprp_united@eprp-ihapa.com**

ተገደሉ። ለሕዝበ-ክርስቲያኑ ሰላምን የምትሰብከው ቤተክርስቲያን ሰላም በውስጧ ጠፍቶ ለ27 ዓመታት ስትታወክ ኖረች።

የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችንም መንግሥት ተብዬው ከሁለት በመክፈልና በመካከላቸው ከፍተኛ ብጥብጥን በማስነሳት፣ አንዱን ክፍል ወግኖ ሌላኛውን በተከበረው መስጅድ ውስጥ ወታደሮች አሰማርቶ አማኞችን ጨፈጨፈ። መብታችን ይከበር ያሉትን በግፍ እስርቤት ወርውሮ ለዓመታት አሰቃያቸው። ሰላም የሚሰበክባቸው ቤተ-ዕምነቶች ሰላም አጥተው፣ አገዛዙ መዕምናኑ እርስ በእርስ እንዳይተማመኑ የካድሬ ሰላዮችን በውስጣቸው ሰግስጎ ሲያፋጃቸው ቆየ።

ይሁን እንጂ ግፍ ያንገፈገፈው የሕዝባችን የትግል ውጤት የሆነው የዶ/ር አብይ አመራር ሰላምና ይቅር ባይነት በሀገራችን ውስጥ እንዲሰፍን ጥረት በማድረጉ፣ ሆድና ጀርባ ሆነው የኖሩት ሲኖዶችና መጅልሶች በመሃላቸው ዕርቀ-ሰላም አውርደው ምዕመኖቻቸው ሰላማዊ ኑሯቸውን መኖር ጀምረዋል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁሉ ያሰደስተና ያስደመመ እርምጃ ነው።

ኢሕአፓ (አንድነት) በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲመጣ ታግሏል፣ ከፍተኛ ዋጋም ክፍሎበታል። ታሪክ ምስክሩ ነው፣ ባሰራጫቸው መግለጫዎችና የጥናት ጽሁፎችም በግልጽ የተቀመጡ ናቸው። በመሆኑም ኢሕአፓ (አንድነት) የተወሰደውን የሰላም እርምጃ ያደንቃል፣ እንቅስቃሴውንም ሙሉ በሙሉ ይደግፋል

እነዚህ ሁለት ታላላቅና ታሪካዊ የእምነት ቤቶች ከጸሎት ቤትነታቸው አልፈው ለሀገር ሰላምና ፍቅር የሚሰበክባቸው ቦታዎች በመሆናቸው፣ ለሀገሪቱ መሠረቶች ናቸው። እንደ ዕምነት ቤትነትም ያለ ምንም የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አስተምሯቸውን እንደሚቀጥሉ ኢሕአፓ (አንድነት) ያለውን ጽኑ እምነት በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ ይወዳል። ይህ የተጀመረው የአንድነትና የፍቅር ሂደት እንዲያድግና ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ሁሉ ሊደግፉትና ሊንከባከቡት ይገባል።

ሰላምና ዴሞክራሲ የሀገር ዋልታ ነው!

P.O.Box 91384 Phone: 202- 241 2078
Los Angeles, CA 90009 eprp_united@eprp-ihapa.com